የውጭ፡አገር፡የነፃ፡ትምህርት፡በቋንቋችን፡እንዳናሥብ፡አድርጐናል።

ኢትዮጵያ፡በምሳሌነት፡የማይወሰን፡የእግዚአብሔርን፡ግዛት፡ይገልጣል።ኢትዮጵያ፡እጆቿን፡ወደ፡እግዚአብሔር፡እንደምትዘረጋ፡ተተነበየ።

*(መዝ፡-፷፯፡፴፤፹፰-፴።ሕዝ፡-፴፡፴-፴፱

ኦሞ፡-፴፡፯።ሶፎ፡-፪፡፲፪)።

ውስጣዊ፡የትምህርት፡አመሠራረትና፡የውጭ፡አገር፡የነፃ፡ትምህርት፡በቋንቋችን፡እንዳናሥብ፡አድርጐናል።ከፊኛ፡ክፍል፡እስተ፡መካነ፡አዕምሮ፡በቋንቋችን፡ያለ፡መማራችን፡ችግር፡አስተሣሠባችን፡የውጭ፡አገር፡ትምህርትና፡ባሕል፡ተገዥ፡አድርጐ፡አገር፡ወላድ፡ምሁሮቻችንን፡ላለማክበር፡ደንቃራ፡ሆኖብናል፡ብንል፡ስሕተተኞች፡ነን፡የሚል፡ግምምት፡የልለንም።ምክንያቱም፣ስሞቻንንና፡ታሪካችንን፡ሰምተውና፡ተመልክተው፡የውጭ፡ዜጐች፡የፈለጋቸውን፡ስሕተት፡ሲፈጽሙ፡እያወቅን፡አናርማቸውም።እንዲያውም፡ልክ፡አንደ፡ሕፃናት፡ሲናገሩ፡እንደምንሥቀው፡ሁሉ፡ለእነሱም፡እየሣቅን፡እናደፋፍራቸዋለን፡እንጂ፡ስሕተታቸውን፡አናርመውም።የእነሱን፡ባሕልና፡ወግ፡ማዕረግ፡አጥንተን፡እንድናደንቅ፡የሚያደርግ፡ሥርዓተ፡ትምህርት፡በማዘጋጀት፤ከእኛ፡ባሕልና፡ሥነ፡ሥርዓተ፡ትምህርት፡ጋራ፡ሊመጣጠን፡በማይችል፡ሁኔታ፡ስለ፡ተማርን፡ሀርገራችን፡በተፈለገው፡ዕቅድና፡አስተሣሠብ፡ሥልጣኔዋን፡ማራመድ፡አልተቻለም፡በሚል፡ስሌት፡ነው።እንዲያውም፣አዕምሯቸው፡ብሩኅ፡የሆኑት፡ወገኖቻችን፡በዓለም፡አቀፍ፡ድርጅቶች፡ሥራ፡እዬ፡ተሠማሩ፡መሥራትን፡በሚመርጡበት፡አኳኋን፡ታቅዶ፡ሀገራችንን፡የምሁራን፡እጥረት፡ችጋር፡እንዲያሰቃያት፡በመደረጉ፡ነው።ታዲያ፡ጥፋቱ፡የግለ፡ሰቡና፡የሀገሪቱ፡አስተዳደር፡ጉድለት፡ወይም፡ድክመት፡እንጂ፡ለምን፡የነፃ፡ትምህርት፡መሰጠቱን፡ተቃወማችሁ?።ብንባል፣መልሳችን፡መቃወማችን፡ሳይሆን፡ያስከተለውን፡መዘዝ፡ሕዝብ፡እንዲረዳው፡በማሠብ፡መፍትሔ፡እንዲገኝለት፡ለመመልከት፡ነው፡ብለን፡እናሥባለን።ሆኖም፣በቋንቋችን፡በምንማርበት፡ግዜ፡የበለጠ፡ሁኔታውችን፡ተረድተን፡ለሕዝባችን፤ንቃትና፡ለሀገራችን፡ብልፅግና፡መፋጠን፡እንደ፡እሚረዳና፡አቋራጭ፡መንገድ፡እንደሚያስገኝ፡ከቀደሙ፡አገሮች፡ልምድ፡ያየነውንና፡ያነበብነውን፡አወንታዊ፡አበለፃፀግ፡አስተውለን፡ስለ፡ተረዳን፡ነው።እና፣ይህ፡ትውልድ፡የግዜውን፡ችግር፡አልፎ፡ከዕለት፡ጉርሱ፡ባሻገር፡ለወደፊት፡ዘለቄታ፡ያለውን፡ዕውቀት፡ገብይቶ፡ሀገሩ፡ወስጥ፡ተደስቶ፡የሚኖርበትን፡እንዲያልም፡እንመኛለን።

የነፃ፡ትምህርት፡መሰጠቱን፡ትቃወማላችሁ፡ወይ?።የሚል፡ጥያቄ፡ቢመጣብብን፡አንቃወምም፤ነፃ፡ትምህርት፡የምንማርባቸው፡አገሮች፡ለፈሊጣዊ፡(ለፖለቲካዊ)፡ጥቅማቸው፡ሲሉ፡አዕምሯችንን፡አጠባ፡(ብሬን፡ወሽ)፡እደሚሉት፡ለቁሳቁሳዊ፡ጥቅም፡ማለትም፡ተቀጥሮ፡ደመ፡ወዝ፡ለማግኛ፡ብለን፡እራሳችን፡ባላወቅነው፡ስልት፡ተዘፍቀን፡ለትውልድ፡ሀገራችን፡ለማሠብ፡አላስቻልንም፡በሚል፡ነው።

ስለዚህ፣ዘአቢሲኒያ፣ዘሐበሻ፣ሐበሻ፣ኩሽ፣ባንዳ፣ካዛንቺስ፣መርካቶ፣ፒያሳ፣ባንዲራ፣ወ.ዘ.ተ.... በአጠቃላይ፡በውጭ፡ቋንቋ፡ሲጠሩን፡መቀበል፡አይኖርብንም።በእንደዚህ፡የመሳሰሉት፡የውጭ፡ዜጋ

ወች፡ከጻፏቸው፡እየገለበጥን፡የምንጠቀም፡ሁሉ፡አኩሪና፡ነባር፡ኢትዮጵያውያንነታችንን፡እያበላሹት፡መሆኑን፡ልንገነዘበው፡ይግባል።የነርሱን፡ቋንቋ፡በምንነጋርበት፡ወቅት፡በጣም፡ትንንሽ፡ስሕተት፡እንኳ፡ስናደርግ፡አያልፉንም።ያውም፡ከአሳፋሪ፡ሣቃቸው፡ጋራ።ያ፡ማለት፡የቋንቋቸውን፡የበላይነነትም፡ሆነ፡እኛን፡ለማሳነስ፡ካልላቸው፡ፍላጐት፡የተነሣ፡ነው።ግዕዝ፡ፊደላችን፡የመጀመሪያው፡የዐዳም፡ቋንቋና፡ፊደል፡መሆኑን፡አልማወቃቸው፡ወይም፡ላለማውቅ፡ወስነው፡ይሆናል፡እንጂ፡ለእነሱም፡ቋንቋ፡ያበደረና፡ትርጉሙም፡የመጀመሪያ፡ማለት፡እንደሆነ፡ማወቅ፡በተገብባቸው፡ነበረ።በሌላ፡አቅጣጫም፡ስንመለከት፡ኢትዮጵያውያን፡ሊቀ፡ምሁሮቻችን፡ሊያሳውቋቸው፡በተገብባም፡ነበረ፡ብለን፡እናሥባለን።

ለምሳሌ፡-የአመሪካ፡መንግሥታት፡፴፪ተኛው፡ርዕሰ፡ብሔር፡ክቡር፡ፍራንክሊን፡ዲ፡ሮዝቬልት፡አካለ፡ስንኩል፡በተሽከርካሪ፡ወንበር፡ይጓዙ፡ነበረ።ይህ፡ሆኖ፡ሳልለ፡አካለ፡ስንኩሉ፡ሩዝበልት፡ተብለውም፡አይጠሩም፡ነበረና፡እኒህን፡ጀግና፡መሪ፡ለመውቀስ፡ሳይሆን፡በአርኣያነታቸው፡ለማመዛዘን፡ስለ፡ከጀለን፡ታሪካቸውን፡እንሆ!፡.....ክቡር፡አቶ፡ፍራንክሊን፡ዴላኖ፡ሮዝቬልት፡የተባበሩት፡አመሪካ፡መንግሥታትን፡ለመምራት፡በ፲፱፻፳፬፡ዓመተ፡ምሕረት፡ተመርረጡ።በዓመቱ፡፲፱፻፳፭፡የግድያ፡።ሙከከራ፡ተደርጐባቸው፡ሕይወታቸው፡ተርረፈ።ግዜው፡የሁለተኛው፡ዓለም፡ጦርነት፡መጀመሪያ፡ስለ፡ነበረ፡ከፍፍተኛ፡የምጣኔ፡ሀብት፡ቀውስ፡ነበረባቸው።በቆራጥነታቸው፡ግን፡የአመሪካ፡ሕዝብ፡በተስፋ፡በርትቶ፡እንዲሠራ፡በማበረታታት፡አገራቸውን፡ከውድቀት፡አዳኑና፡ዝነኛ፡ሆነው፡ታወቁ።ከዚያም፡ወደ፡ግራ፡አመለካከት፡ያላቸው፡ምክትላቸውን፡ክቡር፡አቶ፡ሄንሪ፡ዋላስን፡ሽረው፡የሕግ፡መወሰኛ፡አባል፡የሆኑትን፡ክቡር፡አቶ፡ሔሪ፡ኤስ፡ትሩማንን፡ተክተው፡ከምርጥ፡አማካሪዎቻቸው፡ጋራ፡በተከታታይ፡ዐራት፡ግዜ፡ተመርጠው፡ለዐሥራ፡ሁለት፡ዓመታት፡እንደ፡መሩ፡በድንገት፡ናላቸው፡ውስጥ፡ደም፡ፈስሶ፡ቢሯቸው፡ውስጥ፡ዐረፉ።ታዲያ፡እኒያ፡የተከበሩ፡መሪ፡በተሽከርካሪ፡ወንበር፡በሕዝብ፡ፊት፡ሲሽከረከሩ፡ላለመታየት፡ተጠንቃቂ፡ሰው፡ነበሩ።

“He was elected in 1932. Assuming the Presidency at depth of the Great Depression, Franklin Delano Roosevelt helped the American people regain faith in them. He brought hope as he promised prompt vigorous action, and asserted his Inaugural address, “the only thing we have to fear is fear itself”. The “country asks for actions, and action now. Our greatest primary task is to put people to work”. Though dearly ailing, he was leading the nation as the time of war. He used wheelchair, but he was careful never to be seen in it in public. In February 1933, Roosevelt escaped an assassination attempt. He dumped his left-leaning vice president, Henry Wallace, in favor of Senator Harry S. Truman, and together they won the race. He brought in team of first-rate thinkers, and drew on their ideas as he saw fit”. ከዚህ፡የምንገነዘበው፡ቢኖር፡ጠንካራ፡ሀገርና፡ወገኑን፡ወዳድ፡መሪና፡አዳምጦ፡ተባባሪ፡ሕዝብ፡ከተባበሩ፡የተሳክካ፡ብልፅግናና፡ማናቸውንም፡ችግር፡ተቋቁሞ፡ማሸነፍ፡እንደሚቻል፡ነው።አመሪካኖችም፡ጥቅማቸውን፡ለማስከበር፡ያልላቸው፡ብልጠት፡ጥልቅ፡መሆኑን፡ያመለክታል።ጥቅማቸውን፡ለማያስጠብቅ፡ጉዳይ፡ተጨንቀው፡በነፃ፡የሚቸሩት፡እንደ፡ሌለ፡በሚገብባ፡ማጤን፡ተገቢ፡ነው።

ኢትዮጵያዊው፡የክብርት፡ኢትዮጵያዊቷ፡ንግሥት፡ኅንደኬ፡በጅሮንድ፡ባለ፡ሥልጣንና፡ክርስትናን፡ተጠምቆ፡ወደ፡ኢትዮጵያ፡ለመጀመርያ፡ግዜ፡ያስገብባው፡ክቡር፡ምሉክ፡ግን፡“ጃንደረባው”፡እዬ፡ተባለ፡በመጽሐፍ፡ቅዱሱ፡ሳይቀር፡እስታሁን፡ይጠርራል።ትክክለኛ፡መጠሪያ፡ስሙም፡”ባኮስ”፡ነው።ሙሉ፡ስሙንም፡ስላልተጻፈልን፡ወደ፡ፊት፡ባለ፡ሙያ፡ታሪክ፡መዝጋቢዎቻችን፡አፈላልገው፡ጽፈው፡እንዲያሟሉልን፡እንማፀናለን።እናም፣ከላይ፡በዘርዘርናቸው፡ስሞች፡ኢትዮጵያውያንን፡ሲጠሩን፡ጥቁርነታችንንና፡ኅብረ፡ቀለማምነታችንን፡በማጋነን፡የዝቅተኛነት፡ስሜት፡እንዲስሰማን፡የታቀደ፡ዓረባዊ፡ተንኮል፡በመሆኑ፡ልናወግዘውና፡ትክክለኛ፡መጠሪያችንን፡ማስተማር፡ይግገባናል።ስሞቻንን፡አሳስተው፡

ሲጠሩንም፡ማረም፡እንጂ፣“ውሸት፡ተደጋግሞ፡ሲነገር፡ዕውነት፡ይሆናል”፡ዓይነት፡በዘልማድ፡የወረስነ
ውን፡መጥፎ፡ትሑታዊ፡ኀላ፡አስቀር፡ልማድ፡ማስወገድ፡አልለብን።በሀገራችን፣በባሕላችን፣በቋንቋችን፣
በታሪካችን፣በፊደላችንና፡በመልካችን፡ልንኮራበትና፡አንገታችንን፡አቅንተን፡የምንራመድበት፡ድፍረት፡
ሊለዬን፡አይገብባም።የእኛን፡መልክ፡ለይተው፡ለማውራት፡ክርፈልለጉ፡መታወቅ፡የነበረበት፡-“በውኑ፡
ኢትዮጵያዊ፡መልኩን፡ወይም፡ነብር፡ዝንጉርጉርነቱን፡ይለውጥ፡ይችላልን?”።*ትንቢተ፡ኤርምያስ፡፲፫፡፳፫።እንደ፡
ተባለው፡ውበታችንን፣ባሕላችንን፣ቋንቋችንን፡ወ.ዘ.ተ.....ባጠቃላይ፡ሕልውናችንን፡እያበላሹት፡
እንደ፡ትክክለኛ፡መቀበል፡ያክትም።ዛሬ፡ዓለማት፡በደቂቃ፡መርረጃ፡የሚለዋውጡበት፡ወቅት፡ስለ፡ሆነ፡
እዬ፡ተማማርን፡ስሕተቶቻንን፡እናርማቸው።እናጐልብታቸው።እናስተዋውቃቸው።እንጠቀምብባቸ
ው።ከአጉል፡ዐመል፡ጋራ፡አንቀይጣቸው።ለሰው፡ልጆች፡ቀና፡ባህርይ፡መታረሚያ፡አርአያ፡እናድርጋቸ
ው።የውጭ፡ዜጋ፡ስለ፡አገርና፡ወገናችን፡የጻፏቸውን፡ስናነብብ፡ነጭ፡ከጻፈው፡ስሕተት፡እንደሚኖረው፡
ለመገንዘብ፡ሰው፡መሆናቸውን፡እንጂ፡በአዕምሯችን፡በዘዴ፡የከተቱብንን፡የባላይነትና፡የበታችነት፡አመ
ልካች፡ቅጽል፡መጠሪያ፡ሠርዘን፡አንዱን፡ከሌላው፡በማመሣከር፡ትክክለኛነቱን፡ካረጋገጥን፡በኋላ፡እን
ጂ፡አንድ፡መጽሐፍ፡በማንበብ፡ብቻ፡በዕውነተኛ፡መረጃነት፡አንፈርጀው።በተለይ፡ታሪካችንን፡ለመጻ
ፍ፡የሚወድ፡የውጭ፡ዜጋ፡ከአገር፡ተወላጅ፡ምሁራን፡ወገኖቻችን፡ጋራ፡የተማከረ፡መሆንና፡አለመሆኑ
ን፡እርግጠኛ፡ለመሆን፡ማረጋገጥ፡ግድ፡ይሏል።

ሠለጠንን፡የሚሉ፡አገሮች፡አልፎ፡ተርፎ፡ቋንቋቸው፡እዬተመናመነ፡እንዳይሄድና፡በእንግሊዝኛ
ው፡ተዘንቆ፡እንዳይጠፋ፡ሕግ፡አውጥተውና፡የቋንቋ፡ዘበኛ፡አቋቁመው፡በመከላከል፡ላይ፡ናቸው።እኛ
ም፡የመጀመርያው፡የዐዳም፡ቋንቋችን፡ግዕዝን፡የሚያስከብር፡ሕግ፡ለማውጣት፡ማሰላሰል፡አልለብብ
ን።ሰንደቅ፡ዓላማችንን፡በተመለከትም፡አብዛኞቻችን፡ታሪካዊ፡አምመጣጡን፡በሚገብባ፡ካለመርረዳ
ት፡ሊሆን፡ይችላል!፡በዘፈቀደ፡ባንዲራ፡የምንለውም፡አንጠፋም።ይህ፡የውጭ፡አገር፡ጠላት፡ቋንቋ፡የም
ልክታችንን፡ምንነት፡ድምጥማጡን፡ለማጥፋት፡ታቅዶ፡እንጂ፣ነፃቷን፡አስከብብራ፡ለምትኖር፡ሀገረ፡ግዕ
ዝ፡(መጀመሪያ፣ተቀድዳሚ)፣ሀገረ፡እግዚአብሔር፡ተብላ፡ለመትትደነቀው፡ኢትዮጵያ፡እናት፡አገራች
ን፡ምልክት፡መጠሪያ፡ሊሆን፡አይገበውም።

የሰንደቅ፡ዓላማችን፡አጀማመር፡በኖኅ፡ዘመን፡የጥፋት፡ውኃ፡ማክተሚያ፡ምልክት፡በሰማይ፡
ከታዩት፡የረቀቁ፡ቀስተ፡ደመና፡ኅብረ፡ቀለማት፡ለዓይን፡ጐላ፡ብለው፡ከታዩት፡አረንጓዴ፣ቢጫና፡ቀይ፡
የተወረሱ፡ሲሆኑ፡-አረንጓዴው፡ልምላሜን፣ቢጫው፡ሃይማኖት፡(የእምነት፡ጥንካሬን)፣ቀዩ፡ሀገርን፡
ለማስከበር፡የፈሰሰን፡(የሚፈስስን)፣ደም፡(ቆርራጥነትን፣ጀግንነትን)፡ትርጉም፡የያዙ፡ናቸው።ሰንደቅ፡
ስንልም፡መያዣውን፡(መስቀያውን)፡እንጨት፡ወይም፡ሌላ፡ጠንካርራ፡መስቀያ፡ወይም፡ማውለብለቢ
ያ፡ነው።ዓላማ፡ማለት፡ምልክት፡ሲሆን፡አረንጓዴ፣ቢጫና፡ቀዩ፡የክብር፡ጨርቅ፡ነው።የኢትዮጵያን፡መ
ንግሥት፡በማገልገል፡ላይ፡የነበሩት፡መሪዎች፡ግን፡በመካከሉ፡አንበሣ፡ምሥል፡አስቀምጠው፡“ሞዓ፡
አንበሣ፡ዘእምነገደ፡ይሁዳ”፡የሚል፡ጽሑፍ፡ተጨምሮበት፡ይጠቀሙበት፡ነበረ።አባብሉን፡ላልተማረ
ው፡ሕዝብ፡ለሥልጣነቸው፡ማረጋጊያና፡መስበኪያ፡ተጠቀሙበት፡እንጂ፡የሰሎሞን፡ሥርወ፡መንግሥት
ነት፡አመጣጥን፡አይመለከትም።የሚመለከተው፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ነው።“ሞዓ፡አንበሣ፡የተባለው፡
እርሱ፡ነው።መይሣው፡ካሣ፡ዳግማዊ፡ዐፄ፡ቴዎድሮስም፡ከሰሎሞን፡ሥርዎ፡መንግሥት፡የሌላቸው፡ይ
ጠቀሙበት፡ነበረ።“በአጭር፡ቋንቋ፡አንበሣው፡አስከ፡ዘውዱና፡መስቀሉ፡የራሱ፡የባለቤቱ፡የኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡ምልክትና፡ሥዕል፡ነው።ከዚህ፡ሌላ፡አንዳችም፡ትርጉም፡የለውም።የኢትዮጵያንና፡የእግዚ
አብሔርን፡ጠባቂነትና፡አምላካዊነት፡አምና፡የተቀበለች፡ጥንታዊትና፡የአዳም፡መገኛ፡ምድረ፡ኤዶም፡
ኢትዮጵያ፡ናትና፡ነው።ይህ፡ምልክት፡የኢየሱስ፡የትንቢት፡ስሙና፡መገለጫው፡ብቻ፡ነው”።*ገጽ፡፭፣
በሃይማኖት፡ካባ፡የሚሠራ፡ደባ።በሊቀ፡ምሁር፡ለይኩን፡ብርሃኑ።መስከረም፡፳፪፡ዓመተ፡ምሕረት።

“ሞዓ፡አንበሣ፡ዘእምነገደ፡ይሁዳ”።{እንሆ!፡ከይሁዳ፡ነገድ፡የሆነው፡አንበሣ፡ድል፡ነሥቷል።ዮሐ.ራእይ፡፭-፭}፡የሚለውን፡ቃል፡ለሰሎሞና
ዊው፡ሥርወ፡መንግሥት፡መለያና፡መታወቂያ፡እንደ፡ሆነ፡ብቻ፡ተደርጎ፡በስሕተትና፡በዘልማድ፡ግንዛ
ቤ፡ተወስዶበት፡ኖሯል።*ገጽ፡፭፣እንደ፡ላይኛው።

ከዜናማርቆስ፡መርሐ፣ካናዳ። zienamarqos@yahoo.com

ኢትዮጵያ፡ለዘላለም፡ትኑር።